# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ነሐሴ 26 ቀን 2004 ዓ.ም

### ኢሕአፓ 5ኛ ጠቅላላ
### ጉባኤውን በተሳካ ሁናቴ አጠናቀቀ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ከነሐሴ 23 እስከ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. ከተለያዩ አህጉራት የተወከሉ የፓርቲው አባላትና አካላት በተገኙበት አካሂዷል። ጉባዔው የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፖለቲካ፤ የማህበራዊና የኤኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን እንዲሁም ድርጅታዊ ነክ ጉዳዮችን በስፋትና በጥልቀት ከተወያየ በኋላ የተለያዩ ውሳኔዎችን በማሳለፍና መመሪያዎችን በመስጠት በተጨማሪም ለሚቀጥሉት የሥራ ዘመን የሚያገለግሉ የአመራር አባላትን በመምረጥ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

የኢሕአፓ 5ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የተካሄደው ሀገራችን ኢትዮጵያ ሕልውናዋ ጭምር በአምባገነኑ የወያኔ ዘረኛና ጎሰኛ ቡድን ከምንጊዜውም በበለጠ አደጋ ላይ በወደቀበት ፤ ፖለቲካዊ፤ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ቀውሶቹ ተባብሰው ይህ ነው የማይባል ደረጃ ላይ በደረሱበት፤ አገዛዙ ከውስጥና ከውጭ አድሃሪ ኃይሎች ጋር በመተባበር የሕዝባችንን የዴሞክራሲና የመብት ጥያቄዎች ደብዛ ለማጥፋት በሚሯሯጥበትና መጠነ ሰፊ የሆነ የፕሮፓጋናዳ ውዥንብር እየነዛ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ የሚደርሱበትን ጥቃቶች ተቋቁሞ የውስጥ ችግሮቹንም አስወግዶ የዕለት ተዕለት ተግባሩን በተረጋጋ ሁናቴ እያከናወነ ባለበት ሁናቴ ነው። ጉባዔው የተካሄደው ፓርቲው የተመሰረተበትን 40ኛ አመት ለማክበር በመዘጋጀት ላይ መሆኑ ጉባኤውን ታሪካዊ አድርጎታል።

ይህ ጉባዔ ኢሕአፓ በወያኔም ሆነ የርሱ አምሳያ በሆኑ ፀረ ሕዝብና ፀረ አንድነት ኃይሎች የሚደርስበትን ጥቃት እየተከላከለ ባለበትና፤ ብሔራዊና ዴሞክራሲያዊ ትግሉን በአይበገሬነትና በፅናት እየታገለ በሚገኝበት ሁኔታ የተካሄደ ሲሆን ፍፁም መግባባትና የሃሳብ አንድነትን ባንጸባረቀ፤ ጥንትም፤ አሁንም፤ ወደፊትም የማንነቱ መገለጫ የሆነውን ኢሕአፓዊነትን **በተላበሰ** መልኩ የተካሄደ ድርጅቱም ከምንጊዜውም በበለጠ ተጠናክሮና ራሱን በአዲስ የትግል መንፈስ አድሶ የወጣበት ጉባዔ ነበር።

ጉባዔው የሥራ ዘመኑን በጨረሰው አመራር አካል የቀረበለትን የሥራ ዘገባ ማለትም የተከናወኑ ተግባራትን፤ ያጋጠሙ ችግሮችን እንዲሁም የታዩ ድክመቶችን በሁለገብ መልኩ የዳሰሰውን ሪፖርት የመረመረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በሀገራችን በተለያዩ አካባቢዎች እየታዩ ያሉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በርካታው ሕዝብ ለሕዝባዊ አመፅ እየተገፋፋ መሆኑን የሚጠቁሙ ሁኔታዎች መሆናቸውን ተገዝበ ይህን ትግል ለማፋፋም አመቺ የሚሆኑ የተግባር ውሳኔዎችንም ያሳለፈበትና የወደፊት እቅዶቹንም የነደፈበት ነበር።

ከሁሉም በላይ ኢሕአፓ ላለፉት በርካታ ዓመታት ሕዝባዊ ትግሉ ፈሩን እንዳይለቅ ያደረጋቸው አቅጣጫ የማስያዝ ቅስቀሳና የማደራጀት ተግባሮቹ መልክ የያዙበት በመሆኑ፤ እንዲሁም በወያኔ አገዛዝና በሕዝቡ መካከል ያለውን የማይታረቅ መሠረታዊ ቅራኔ ለማስወገድና የወያኔን አገዛዝ ለመጣል ለሀገር አንድነትና ለዴሞክራሲ ከቆሙ ኃይሎች ጋር ለመተባበር ያደረገውን ጥሪ በዚህም ጉባዔ በማጠናከር በአዲስ ለተመረጠው የድርጅቱ አመራር ይህንን ውሳኔ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችልበትን እቅድ አውጥቶ እንዲንቀሳቀስ መመሪያ ሰጥቶታል።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA

E-mail : ESPIC@aol.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

በመጨረሻም ጉባኤው በተወያየባቸው ጉዳዮች ላይ ጠቅላላ ውሳኔዎችን በማጽደቅና ስሜት ቀሳቃሽና የማንነቱ መግለጫ የሆነውን „የትግሉ ነው ሕይወቴ“ የተባለውን መዝሙር በደመቀ ሁኔታ በመዘመር በጥሩ ሁኔታ ተጠናቋል።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!

በትግላችን እናቸንፋለን!!

ኢሕ አፓ ይለምልም!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA

E-mail : ESPIC@aol.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France